በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## የካቲት ፲፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# <u>መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን</u>

- ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይሰማችኋል?

- በዛሬው ሥልጣኔ የተስፋፋበት ዓለምስ ተፈላጊነት አለው?

## <u>*ይህንን እናድርግ*</u>

- በቤታችን ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስ ይኑረን።

- ዘወትር መጽሐፍ ቅዱስን እናንብብ።

- ሕይወታችን በመጽሐፍ ቅዱስ የታገዘ ይሁን።

- በተግባር በማድረግ መጽሐፍ ቅዱስን እንኑረው። ልበ አምላክ ዳዊት "አንተ እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።" እንዳለ። <u>*መዝ 118፡11።*</u>

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

- አንድን ጥቅስ ብቻ መሠረት በማድረግ ጽንሰ ሐሳብንም ይሁን ተግባርን የምንገነባ አንሁን፡፡ ለምሳሌ "ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ፡፡" *1ኛ ጢሞ 5፡23፡፡*

- ቅዱስ ጳውሎስ "ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፡፡" ብሎናል፡፡ *2ኛ ቆሮ 3፡6፡፡*

- ቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ቋንቋ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃልና መለኮታዊ እስትንፋስ ነው ብሎታል፡፡ "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡" *2ኛ ጢሞ 3፡16-17፡፡*

# መጽሐፍ ቅዱስ ና ቤተ ክርስቲያናችን

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) ምንጩ መጽሐፍ ቅዱስና ምንጩ ትውፊተ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡

- በብርሃን ወይም በጨለማ የምንጓዝ መሆናችንን ለይተን የምናውቅበት ወይም የምንለካበት መለኪያችን ነው፡፡

- **በውስጣችን ጥልቅ ተጽእኖ የሚያሳድር የሚለውጠንም ታላቅ ኃይል ያለው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡**

- "ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር፡፡ … ጃንደረባውም፡፡ እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው? አለው፡፡ ፊልጶስም፡፡ በፍጹም ልብህ ብታምን፥ ተፈቅዶአል አለው፡፡ መልሶም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ፡፡ ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፥ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ፥ አጠመቀውም፡፡ ፡፡" *የሐ ሥራ 8፡26-38፡፡*

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

- ቅዱስ ጳውሎስ ዳግመኛ "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል።" ብሎናል። *ዕብ 4፡12።*

## *መጽሐፍ ቅዱስ ና እኛ ኦርቶዶክሳውያን*

- መጽሐፍ ቅዱስ ስሜታችንን፣ አመለካከታችንን በመግለጽ ሕይወታችንን ከአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ጋር ያነጻጽራል።

- ጌታችንም "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።" ብሎናል። *ዮሐ 5፡39።*

- ቅዱስ ጳውሎስም "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። ።" *ቆላ 3፡16።*

*የሚከተሉትን ነጥቦች በዝርዝር እንመልከታቸው*

1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው
2. የመጽሐፍ ቅዱስ በረከቶች
3. መጽሐፍ ቅዱስን ስለምን እናጠናለን?
4. የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እናጥና?
5. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና መጽሐፍ ቅዱስ
6. መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## *መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው*

- እስከዛሬ ከተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ የሚበልጥ ታላቅ መጽሐፍ ነው።

- በመጽሐፉ እግዚአብሔር ራሱ ለሰው ይናገራል።

- መለኮታዊ መመሪያ የሚገኝበት መጽሐፍ ነው።

- መጽሐፉ የእግዚአብሔር ስለሆነ የሚከተሉትን ይሰጣል።
    - ከሐዘን መረጋጋትን
    - ግራ በተጋባን ጊዜ ትክክለኛ አቅጣጫን
    - ለችግራችን ትክክለኛ ምክርን
    - ለኃጢአታችን ተግሳጽንና
    - ለየዕለቱ መሻታችን ወይም ጥረታችን መበረታታትን፣ እገዛን።
- መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ተራ መጽሐፍ አይደለም። ነገር ግን ታሪክን፣ ምሳሌን፣ መዝሙራትን፣ ትንቢቶችን፣ ፍልስፍናን፣ ፈጠራን፣ ወዘተ በአንድ ላይ ያካተተ ስብስብ ነው።

- መጽሐፍ ቅዱስ ከ 1500 በሚበልጡ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፣ በየዓመቱም ከሌሎች ማናቸውም መጻሕፍት በበለጠ ሁኔታ ብዙ ቅጂ ይሸጣል።

- ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚበዙት በሙሴ፣ በልበ አምላክ ዳዊት፣ በጠቢቡ ሰሎሞን፣ በወንጌላውያን ማቴዎስና፣ ሉቃስ እንዲሁም በቅዱስ ጳውሎስ የተጻፉ ናቸው።

- እነርሱም የራሳቸውን ጽሑፍ አልጻፉም። በነርሱ በመጠቀም የጻፈ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል ጸሐፊ መንፈስቅዱስ ነው።

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

- ቅዱስ ጴጥሮስ "ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።" ብሎናል። *2ኛ ጴጥ 1:20-21።*

- መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና ሀዲስ የሚባሉ ሁለት ኪዳናት አሉት። ኪዳን ውል፣ ስምምነት ማለት ነው።

- መጽሐፍ ቅዱስ 81 ነው። 46 ቱ የብሉይ ሲሆኑ 35ቱ የሐዲስ ናቸው።

- መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው፡-
    - እንደ ዳዊትና ሰሎሞን ባሉ ነገሥታት
    - እንደ አሞጽ ባሉ እረኞች
    - እንደ ዘካርያስ ባሉ ካህናት
    - እንደ ሳሙኤልና ኢሳይያስ ባሉ ነቢያት
    - እንደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ባሉ ዓሳ አጥማጆች
    - እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ባሉ ሊቃውንት
    - እንደ ቅዱስ ሉቃስ ባሉ የሕክምና ባለሞያዎች ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስ በሲና፣ በይሁዳ፣ በሮም እስር ቤት፣ በፍጥሞ ደሴት፣ በኢየሩሳሌም ወዘተ ተጽፏል።

- ጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎቹ፣ ቦታዎቹ፣ ጊዜዎቹ ቢለያዩም ሁሉም 81 መጻሕፍት በመንፈስ፣ በርዕሰ ጉዳይ በዓላማ ሳይለያዩ አንድ ናቸው።

- የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ማዕከሉ በእግዚአብሔር ያመኑ ሕዝቦች በተለይም እስራኤል ሲሆኑ የሐዲስ ኪዳን ደግሞ ሰው የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## *የመጽሐፍ ቅዱስ በረከቶች*

- የተስፋና የመረጋጋት የምሥራች፡፡ “መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ
- ናቸው፡፡” *ሮሜ 10፡15፡፡*

- ሙሴ ተናነገረ ሕዝቡም አልፈሩም፡፡ *ዘጸአ 14፡13-14፡፡*

- እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእነንናንተ ጋር ነኝ፡፡ *ማቴ 28፡20፣ ሮሜ 8፡31፣ ፊል 4፡13፡፡*

- የሚመራ ብርሃን፡፡ “ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡” *መዝ 118፡105፣ ምሳ 6፡23፣ 2ኛ ጴጥ 1፡19፡፡*

- የሚሠራ ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ፡፡ *ዕብ 4፡12፡፡*

- የእግዚአብሔር ጦር ዕቃ፡፡ *ኤፌ 6፡10-11፣ መዝ 19፡7፣ 1ኛ ጴጥ 1፡13፣ መዝሙር 1፡፡*

- የዕድገትና የፍጹምነት መለኪያ፡፡ “የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡” *2ኛ ጢሞ 3፡16-17፡፡*

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እናጠናለን?

- የሕይወት (የመዳን) መጽሐፍ ስለሆነ፡፡ "በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም፡፡" ***ዕብ 9:22፣ ዮሐ 3:36፣ 1ኛ ዮሐ 5:5፡፡***

- ከሰማይ በታች እንድንበት ዘንድ የተሰጠን ሌላ ስም ስለሌለ፡፡ "መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡" ***የሐዋ ሥራ 4:12፡፡***

- እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ ስለሚለን፡፡ "እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" ***ማቴ 28:20፣ ሮሜ 8:31፣ ፊል 4:13፡፡***

- ለነፍሳችን ምግብ ነውና፡፡ "ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡" ***መዝ 118:105፣ ማቴ 4:4፡፡***

- የመጨረሻው ፍርድ ሕግ የሚገኝበት ስለሆነ፡፡ "የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል፡፡" ***ዮሐ 12:48፣ ሮሜ 2:16፡፡***

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናጥና?

- በመንፈስ እግዚአብሔር ረዳትነት፡፡ “ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ፡፡ ፡፡” *መዝ 118፡18፡፡*

- በሳይንሳዊ መንገድ መተንተንም ሆነ መመርመርን አንሞክር፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ መጽሐፍ ነውና በመንፈስ ፈቃድ እንቀበለው፡፡ “እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ፡፡” *የሐዋ ሥራ 4፡12፡፡*

- እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ ስለሚለን፡፡ “እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?” *ማቴ 28፡20፣ ሮሜ 8፡31፣ ፊል 4፡13፡፡*

- በአክብሮት፡፡ “ገዢዎች በከንቱ አሳደዱኝ ከቃልህ የተነሣ ግን ልቤ ደነገጠብኝ፡፡” “ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን፡፡” *መዝ 118፡161፣ 1ኛ ተሰ 2፡13፡፡*

- በትሕትና፡፡ “እነዚህን ሁሉ እጄ ሠርታለችና እነዚህ ሁሉ የእኔ ናቸው ይላል እግዚአብሔር ነገር ግን ወደዚህ ወደ ትሑት፥ መንፈሱም ወደ ተሰበረ፥ በቃሌም ወደ ሚንቀጠቀጥ ሰው እመለከታለሁ፡፡” *ኢሳ 66፡2፡፡*

- እግዚአብሔር ምን ሊናገረኝ ይወዳል በማለት ለራስ ጥቅም እንደሆነ በማመን፡፡ “ሳሙኤልም፡፡ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለው፡፡” *ቀዳ ሳሙ 3፡10፡፡*

- መጽሐፍ ቅዱስን በቁጥር፣ በምዕራፍ፣ በታሪክ በተገለጹት፣ በርዕሶቹ፣ የቃላቱን ትርጓሜ በማወቅ፣ ሙሉ ትርጓሜያቱን በማጥናት፣ እንደ ቃሉም ለመኖር በመጣጣር ወዘተ ማጥናት ይገባል፡፡

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## መጽሐፍ ቅዱስ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን

- ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱስን በሚከተሉት የተለያዩ መንገዶች ታከብራለች፡፡

1. ዘወትር በመንበርዋ ወንጌሉን በማስቀመጥ፡፡
2. አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሲታነጹ በመሠረቱ ውስጥ ወንጌሉን በማኖር፡፡
3. ቀሳውስቱ ወንጌሉን ከማንበባቸው በፊትም ሆነ በኋላ ታላቅ ክብር ሰጥተው ወንጌሉን በመሳም፡፡
4. ቀሳውስቱ ወንጌሉን ከማንበባቸው በፊት ልዩ የማዕጠንት ጸሎት እየሰገዱ በማድረስ ወይም በማድረግ፡፡
5. ቃሉ ብርሃናችን እንደሆነ ለማስረዳት ወንጌሉ ሲነበብ ሻማ፣ ጧፍ በማብራት፡፡
6. ይልቁኑ ቃሉ የእግዚአብሔር ቃል ነውና ሲነበብ ተነስተን ቆምን እንድንሰማ በማድረግ፡፡

## መጽሐፍ ቅዱስና የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት

1. ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስዶ መጸለይ፡፡ ምሳሌ፡- መዝሙረ ዳዊት…
2. በማኅሌቱ፣ ሰዓታቱ… ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስዶ መዘመር፡፡ ምሳሌ፡- ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል *መዝ 40፡13፡፡*
3. ብዙዎች የቅዳሴ ጸሎት ክፍሎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ እንዲሆኑ መደረጋቸው፡፡ ምሳሌ፡- *ማቴ 13፡16፡፡*
4. በቅዳሴ የሚነበበው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጣ እንዲሆን መደረጉ፡- የዲያቆኑ ምስባክ፣ የልዑካኑ ምንባባት፣ ካህኑ አስቀድሞ የሚያነባቸው ሥርዓቶች…

# መጽሐፍ ቅዱስና ሕይወታችን

## *የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ዶግማ ና መጽሐፍ ቅዱስ*

1. *ሁሉም የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ፣ መሠረቱ በሆነው በትውፊት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።*
2. *ሰው ሆኖ የማይወድቅ የለምና በሰዎች ትንታኔ ወይም ምክንያት ብቻ ላይ የተመሠረተ ዶግማ የላትም። መሠረቷም ሆነ ጉልላትዋ እርሱ እግዚአብሔር ቃሉም ነውና።*
3. *ቅዱስ መጽሐፍ አይወድቅም ብላ ታምናለች። "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና..." 2ኛ ጴጥ 1፤21። "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።" ማቴ 24:35፣ ማር 13:31፣ ሉቃ 21:33።*
4. *ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ ታበረታታለች።*
5. *ሰዎች የየራሳቸው ትርጉም ይዘው እንዲሄዱ አትፈቅድም። ነገር ግን ትውፊተ ቤተ ክርስቲያንን፣ ትምህርትዋንና የአባቶችን ይትበሃል መሠረት በማድረግ ይሄዱ ዘንድ ታስተምራለች። ኢትዮጵያዊው "የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" እንዳለው። የሐ ሥራ 8:31፣ "ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤ ሲተረጉምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያስረዳ። ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር።" የሐ ሥራ 17:2-3።*
6. *ዮሐ 6:35-56፣ ሉቃ 13:3፣ ሉቃ 13:5፣ ማር 16:16፣...*

- *እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን ታጠኑ ዘንድ አበረታቻችኋለሁ። ያልተረዳችሁትም ቢኖር የንስሐ አባቶቻችሁን ጠይቁ።*

ይቆየን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።